“ልብ አንጠልጥሎ እንደ ጀመረ፣ ልብ አንጠልጥሎ የሚጨርስ
የሲድኒ ሼልደን ድንቅ መጽሐፍ!!!”

ዴይሊ ቴሌግራፍ

የፈቅር ሰመመን



THE SILENT WIDOW

ሲድኒ ሼልደን
SIDNEY SHELDON

ትርጉም፡ ብርሀኑ በላቸው

ዓይናም ሰመመን

THE SILENT WIDOW



ሲድኒ ሼልደን
SIDNEY SHELDON

ትርጉም: ብርሀኑ በላቸው

© All Rights Reserved
© መብቱ ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው::

የመጀመሪያ ዕትም ሰኔ 2013 ዓ.ም

ቡክላንድ አሳታሚና አከፋፋይ
0922 74 02 02/ 0930083308

ቅድመ ታሪክ

“እባካችሁን በቃኝ ከዚህ በላይ ስቃይ አልችልም!”

ሽማግሌው አይኖቹን በድንጋጤ ጎልጉሎ እሱ ወደተሰቀለበት እንጨት (ጣውላ) ላይ እየተሸከረከረ የሚመጣውን የድሪሉን ጫፍ ተመለከተ። የሚሸከረከረው የድሪል ጫፍ ሰውነቱን ሰርስሮ፣ አጥንቱን ፈልፍሎ ከጀርባው ላይ ካለው ጣውላ ላይ ሲሰካ ምን አይነት ስሜት ሊሰማው እንደሚችል አሰበና ስቅጥጥ አለው!!

ሽማግሌውን እንደ ክርስቶስ በገመድ ላይ ከጣውላው ጋር የሰቀሉት እና የሚያሰቃዩት ሰዎች አለቃ፣ እነርሱ የፈለጉትን የገንዘብ መጠን ሁሉ ሊሰጣቸው እንደሚችል ያውቃል። ያም ቢሆን ግን ሽማግሌውን የሚያሰቃዩት ሰዎች አለቃ ከሰውዬው ብር ይልቅ ሞቱን ነበር የሚመርጠው።

እዚህ ያረጀ ህንፃ ውስጥ ከሚገኝ መጋዘን ውስጥ ይህ ሽማግሌ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ግራ ገብቶታል። ለቀናት ይሁን ለሰዓታት? በፍፁም ሊያውቅ አይችልም። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ሽማግሌው ከደረሰበት ተከታታይ ድብደባዎች እና ስቃዮች የተነሳ ራሱን በተደጋጋሚ እየሳተ እና እየነቃ ስለነበር ነው። በተለይ ደግሞ እንደወረቀት በተጨማደደ የሽማግሌ ቆዳው ላይ በሲጋራ የተቃጠለው ቦታ እጅግ አድርጎ እየሰበሰበው ስለሆነ ስቃይ በዝቶበታል። የደረት (የጎድን) አጥንቶቹ ተሰባብረዋል። ፊቱ፣ አይኑ እና ከንፈሩም በደረሰባቸው ድብደባ ምክንያት በጣም አብጠዋል። የብልቱ ቆዳ በምላጭ ተቆራርጧል። ብቻ አንድ በሰው ልጅ ስቃይ የሚደሰት ሰይጣናዊ ሰው ሊያደርስ የሚችለው ስቃይ በሙሉ ሽማግሌው ላይ ደርሶበታል። በተለይ ደግሞ ይህንን ስቃዩን በመጋዘኑ ጥግ ላይ ሆና በተንቀሳቃሽ ስልኳ የምትቀርፀው ወጣት ልጅ ሰውነቱ ላይ ከሚደርስበት ስቃይ በላይ ስቃይ ሆኖበታለች። ‘ይህቺ ሽርሙጣ! እንዴት የእኔን ስቃይ ትቀርፃለች’ እያለ በጎን በኩል ያያታል።

የሚሸከረከረው ድሪል ከሽማግሌው አካል በጥቂት ርቀት ላይ ሲደርስ ቆመ። ምናልባትም የስቃይ ሰርከስ ትርኢቱን የሚመራው ትላልቅ ቡናማ አይኖች ያሉት የቡድኑ አለቃ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ሳይደርስ አልቀረም። ሽማግሌው ይህንን የሰይጣን ቁራጭ የሆነ አለቃቸውን በአይኑ እየተለማመጠ “እባክህን!” እያለ በስቃይ ድምፅ ለመነው።

ይሄኔም የድሪሉ ሞተር ተነሳና ጫፉ እየተሸከረከረ የሽማሌውን ሰውነት ሰርስሮ ወደ ውስጥ በመግባት ስራውን ጀመረ። ሽማግሌው በሲቃ ጣእር ተሞልቶ “እባክህን የምትፈልገውን ነገር ሁሉ አደርግልሃለሁ! አ ፈጣሪ!” በማለት እየጮኸ ደምና ፈሳሽ በእግሮች መሀል ወደታች ወረደ።

ይሄኔ ባለ ቡናማ አይኑ አለቃቸው ፈገግ በማለት "ምንድን ነው ያልከኝ?" አለ የጀሮውን ክፈፍ ወደ ፊት ገፍቶ።

"ወዳጄ የድራሉ ድምፅ በጣም ስለሚጮህ አንተ የምትለው ነገር ምንም አይሰማኝም።" አለው።

በኢይኑም ድራሉን የያዘውን ሰው ስራውን እንዲቀጥል አዘዘው። ከሸማግሌው በሚወጣው ደም እና የስቃይ ድምፅም አለቃቸው ውስጡ ተነሳሳ!! ሸማግሌው በድራል ገላው ተሰርስሮ ህይወቱ ካለፈ በኋላ የድራሉ ድምፅ ፀጥ አለ። የሸማግሌውን ስቃይ በሞባይል እንድትቀርፅ ያስገደዳት ወጣት ሴትን ሲያይ ደግሞ ውስጡ በደንብ ተነሳሳ። እርግጥ ነው እሱ ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን መግደል ይበልጥ ያስደስተዋል። ለማንኛውም የማንኛውንም ሰው ህይወት ማጥፋት በጣም ደስ ይለዋል። ምክንያቱም የሰውን ህይወት መንጠቅ እጅግ በጣም የሀያልነት መገለጫ ነው ብሎ ያምናል።

ከመጋዘኑ ግድግዳ ላይ ከሚገኝ ጣውላ ላይ ተንጠልጥሎ ያለውን የሸማግሌውን በድን ሲመለከት በጣም እርካታ ተሰማው። ይሄ ቀሽም ሸማግሌ እኮ ምናልባት ከእሱ እኩል የሆነ ወይንም ከእሱ የበለጠ ሀብት ሊኖረው ይችል ይሆናል።

ግን ይሄው ልክ ከቄራ እንደመጣ ሥጋ ሆኖ ተንጠልጥሏል አይደል? "አለቃ ራሳውን እናውርደው እንዴ?" ብሎ ሸማግሌውን ከሚያሰቃዩት ሰዎች መካከል አንዱ ጠየቀው።

"አታውርደው ተወው!" አለና ወደ ሸማግሌው ራሳ ተራምዶ ከጃኬቱ ውስጥ ብዙ የመቶ ዶላር ኖቶችን አውጥቶ የራሳው አፍ ውስጥ ጎሰጎሰበት።" "ይሄ ደነዝ ሸማግሌ የገደልኩት ለገንዘብ ብቻ አለመሆኑን ቢያውቅ ምንኛ ጥሩ ነበር" በማለት አልጎመጎመ።

ክፍለ አንድ

አንዲት ወጣት አሜሪካዊት የህፃናት ሞግዚት ሚክሲኮ ሲቲ ውስጥ በድንገት ትሰወራለች። ጉዳዩ ለጊዜው ፍትህ ሳያገኝ ቢቀርም የሚያስከትለው ጣጣ ግን እጅግ ከባድ ይሆናል። ከአስር ዓመት በኋላ ሎስ አንጀለስ በአሰቃቂ የግድያ ወንጀሎች መታመስ ጀመረች። ሁሉንም ሟቾች የሚያገናኘው ገመድ አንድ ብቻ ነው። በገዳይም፣ በተገዳይም መረብ ውስጥ የሚገኙት ሁሉም የሳይኮሎጂስቷ ኒኪ ታካሚዎች ናቸው።

የኒኪን ሕይወት ቀረብ ብሎ ላስተዋለ ሰው፣ ሴትዮዋ በክትትል ስር መሆኗ ይገለጥለታል። የምሥጢሩን ቁልፍ ለመፍታት ኒኪ አነፍናፊ የግለሰብ መርማሪ ቀጥራ ስትንቀሳቀስ ማወቅ ከሚገባት በላይ ምስጢር እጇ ላይ ይገባል። ገዳይ በበኩሉ የኒኪን ፀጥ ማለት ከማንም በላይ ይፈልገዋል። ፍቅሩ፣ ጨዋታውና ግድያው ወደ ሎስ አንጀለስ ጎዳናዎች ያመራል። ትንቅንቁ ድርብርብ፣ ጥልፍልፍሹ ውል አልባ ይሆናል። ምንም ያህል የፍቅር ሰመመን ቢኖር፣ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ እንኳን ወዳጅ ጥላ አይታመንም።







“ሼልደን በአቅሙ ማማ ላይ ሆኖ የሚሰራ ደራሲ ነው።”
ኒውዮርክ ታይምስ

“በሴራ የተሞሉና ልብን ስቅል የሚያደርጉ ታሪኮችን በመጻፍ ሼልደን ወደር የለውም”
አሶሼትድ ፕሬስ



የልብ ወለድ ድርሰቶችን እና የፊልም ጽሁፎችን መጻፍ የጀመረው ዘግይቶ ቢሆንም፣ ሲድኒ ሼልደን በምርጥ የመጽሐፍ ሽያጭ መዝገብ ላይ አውራ ከሆኑት ቀዳሚውን ቦታ የሚይዝ ደራሲ ነው። ለዚህም ደግሞ በዓለም ዙሪያ በብዙ መቶ ሚሊየን ኮፒ መጽሐፎችን መሸጡ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል። ሲድኒ ሼልደን የአስካር፣ የቶኒ እና የኤድጋር ሽልማቶችን በመውሰድ ከደራሲያን መሃል ብቸኛ ነው። በብዙ ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ ጸሐፊ በመባልም ስሙ የዓለም ድንቃ-ድንቅ መዝገብ ላይ መስፈር ችሏል።

ቡክ ላንድ
0922740202

EIDO ADVERT

ዋጋ 220.00 ብር
ዋጋ ሁለት መቶ ሃያ ብር

ተሀ ያዕቆብ ኃ/ሥላሴ 0966777051